Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

የአከባቢ አደጋዎችና የጤና ጠንቆች

# በካርቦን ሞኖኦክሳይድ መመረዝ

## ለመከላከል የሚያገለግሉ መመርያዎች

**ለካርቦን ሞኖኦክሳይድ ከመጋለጥ መከላከል ይችላሉ**

- በየዓመቱ ብቁ በሆነ ባለ ሞያ ቴክኒሻን የእርስዎ የማሞቅያ ሲስተም፣ የውሃ ማሞቅያና ሌላ የሆነ በጋዝ፣ በዘይት ወይም በከሰል የሚሰራ ሲስተም እንዲመረመር ያድርጉ።
- በባትሪ ድንጋይ የሚሰራ የካርቦን ሞኖኦክሳይድ ጠቋሚ እቤትዎ ውስጥ ያስገቡና፣ በየዓመቱ፣ በበጋና በጸደይ ወቅት፡ ላይ ሰዓትዎን ሲቀይሩ፣ ባትሪዎን ቼክ ያድርጉ ወይም ይቀይሩ። ጠቋሚው ድምጽ ካሰማ፣ ቤቱን ባስቸኳይ ለቀው ይውጡና 911 ይደውሉ።
- በካርቦን ሞኖኦክሳይድ መመረዝዎን ከጠረጠሩና መፍዘዝ፣ እራስዎን ማዞር ወይም ማቅለሽለሽ ከጀመርዎ፣ ወዲያውኑ የህክምና እርዳታ ይፈልጉ።
- እርስዎ፣ እቤትዎ ውስጥ፣ ቤዝመንት ውስጥ፣ ጋራዥ ውስጥ ወይም መስኮት አጠገብ፣ ጄነሬተር፣ የከሰል ምድጃ፣ የካምፕ ስቶቭ ወይም ሌላ በቡታ ጋዝ ወይም ከሰል የሚሰሩ ምጅጃዎችን አይጠቀሙ።
- በሩ ክፍት ሆኖ ቢቆይም እንኳን፤ ከቤትዎ ጋር በተጣበቀ ጋራዥ ውስጥ፣ የሰው ወይም የጭነት መኪና ሞተሩን አስነስተው ትተው አይሂዱ። ።
- የአየር መውጫና መግቢያ በሌለው ምድጃ ወይም የእሳት ቦታ ላይ ምንም ዓይነት ነገር አያንድዱ።
- ቤትዎን በጋዝ በሚሰራ ምድጃ አድርገው አያሙቁ።